# *አንዳፍታ ላውጋችሁ*

## *ከጌታቸው ኃይሌ*

*አንባቢን እዲያጫውት አድርጌ ጽፌ አንዳፍታ ላውጋችሁ በሚል ርእስ ያሳተምኩትን የግል ሕይወቴን ካነበቡት ውስጥ በግሌ የደረሰኝ አድናቆት ገርሞኝ፥ ምን አይተውበት ይሆን በማለት እኔም ባለፈው ሳምንት አነበብኩት። ስጽፈው ካየሁት የተለየ ሌላ ምንም አዲስ የሚያስደንቅ ነገር አላገኘሁበትም፤ ያው እንዳሰብኩት አጫዋች ነው። እርግጥ እኔ ባልጽፈው ኖሮ ሳይጻፍ ሳይታወቅ የሚቀር የኢትዮጵያ ታሪክ አለበት።*

*መጽሐፉን* (*አቶ*) *መቆየት መልካሙ ከገመገሙት በኋላ ደግሞ ሁለት ሰዎች* (*ኮማንደር አሰፋ ሰይፉና ዶክተር ታደለ ገ ሕይወት*) *ሐሳባቸውን በይፋ ገልጸዋል። በዚህ አጋጣሚ ገምጋሚውንና ግምገማውን የተቹትን ሁለቱን ሰዎች አመሰግናለሁ። ምክንያቱም፥ በግምገማው ምክንያት "መጽሐፉን እንዴት ነው የምናገኘው?" የሚለው ሰው ቊጥር ጨምሯል። ለእንዲህ ያሉ ጥያቄዎች መልሴ ከዚህ በታች ያለው ነው፤*

*የ. . .* ***አንዳፍታ ላውጋችሁ*** *ዋጋ* (*መላኪያውን ጨምሮ*) *አሜሪካ አገር፡* US$19.95.
*ከአሜሪካ ውጪ* (*በአሜሪካ ገንዘብ*)*፡* US$25.00.

*የመላላኪያ አድራሻ፡*

> PO BOX 113
> Avon, MN 56310
> USA

"*መላኪያውን ጨምሮ*" *ማለት የተጠቀሰው ዋጋ* (US$19.95 *እና* US$25.00) *መላኪያውን ይጨምራሉ ማለት ነው እንጂ* "*መላኪያውንም ጨምሩ*" *ማለት አይደለም። ከአሜሪካ ውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ተጨማሪ ጥያቄ* "*የአሜሪካ ገንዘብ ከየት አምጡ ትለናለህ?*" *የሚል ነው። በየትኛውም የዲሞክራሲ አገር ያለ ሰው አጠገቡ የሚገኘውን ባንክ* "*የአሜሪካ ዶላር ሸጥልን*" *ቢሉት ይሸጣል። ሸቀጡን መኒ ኦርደር* (money order) *በሚባል ቸክ ያስረክባል። ቸኩን ከላይ ወደተሰጠው አድራሻ መላክ ነው።*

*አሁን ዶክተር ታደለ ገ ሕይወት በትችታቸው ውስጥ ስላነሡት አንድ ቁም ነገር* (*ልጅ ከኢትዮጵያ ውጪ ስለማሳደግ*) *የግል አስተያየቴን ልስጥ። ግን ወደዚያ ከመሄዳችን በፊት ከጽሑፋቸው ውስጥ መጀመሪያ ሦስት ነገሮች አብረን እንሰርዝ። አንዱ* "*ዶክተር ጌታቸው የአሜሪካ ዜጋ ሆነዋል*" *የሚለው ነው፤ ዶክተር ታደለ ይኸን መረጃ ከየት አመጡት? እኔ የኢትዮጵያ ፓስፖርቴን በየጊዜው እያሳደስኩ የምኖር የአሜሪካ ጥገኛ፥ የኢትዮጵያ ዜጋ፥ ነኝ እንጂ የአሜሪካ ዜጋ አልሆንኩም፤ ብሆንም ይጠቅመኛል እንጂ ማንንም አልጎዳም ነበር።*

*ሁለተኛው፥* "*የሚገርመው* (*ዶክተር ጌታቸው*) *ልጆቻቸው በአሜሪካዊነታቸው የሚኩሩ ሆነዋል ብለው ጽፈዋል*" *ያሉት ሐሰት ነው፤ አንድም ቦታ እንዲህ ብዬ አልጻፍኩም። የጻፍኩት፥* "(*ልጆቻችን*) *ሁሉም በኅብረተሰቡ ውስጥ የተከበረ ቦታ የያዙ፥ ለተቸገረ የሚያዝኑ፥ ወላጆቻቸውን የሚወዱና የሚያከብሩ፥ ደስተኞች አሜሪካውያን ሆነዋል*" *ነው።*

*ሦስተኛ፥ ዶክተር ታደለ አገር ጥዬ የወጣሁበትን ምክንያት ሲገልጹ የጻፉት እኔን ከአለሁበት አገር ወዳድ ደረጃ የሚያቃልለኝ አነጋገር ነው። እንዲህ ይላሉ፤*

> ዶ/ጌታቸው ቅድስት ማሪያም ሄደዉ ሳንቲም ሲያከፋፍሉ ረሃብተኛው ይወሩቸዋል፡፡ ሳንቲሙን ወደሜዳ በትነው ወደ መኪናቸው ሸሽተው ይገባሉ፡፡ በዚህ መነሾ ያሰቡት ሃገሬን እያስተማርኩና እየጻፍኩ ለመኖር ብመጣ ልብሴን ከላዩ ገነጣጥለው ሊወስዱት ይጋበዛሉ፡፡ ሃገርን ጥሎ መኖር የሚል ድምዳሜ ከአጻጻፋቸው ይከተላል፡፡ የኔ ጥያቄ ስለሃገሩ ምንነት የተጠበበ የእውቀት ጎተራው ዶ/ጌታቸው በኣገሩ በሕዝቡ ምሃል መኖር ካልቻለ ማን ይኑር?

ዶክተር ታደለ፣ ምነው ምነው፥ ወገኑን የሚወደውን ወንድምዎን ምን አይተው እንዲህ ያለ ስም አወጡለት? በአንዲት ገጽ ላይ አስፍረው የበተኑት ጥቃትዎ በዛብኝ፡፡ በቁጭት ያዩት አገራቱ "የእውቀት ጎተራው" ያሉትን ሰው ማጣቷን ሲሆን፥ እኔ አገሬን ወገኔን እንዴት እንዳጣሁና በማጣቴም የተሰማኝን ሐዘን ጽፌው ሳለ አላዩትም፡፡

የሆነው እንዲህ ነው፣ በዓይኔ ያየሁትን ሕዝባችን ያለበትን ችግር ዘርዝሬ፥ ችግሩ የሕዝባችንን ክብር እንዴት እንደነካው በሐዘን ካሰፈርኩ በኋላ፥ ወገኔ ከዚህ ችግር እንዲወጣ በግሌ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አሰላስለው የነበረውን ገጽ 167 ላይ ከዚህ በታች እንዳለው ጽፌው ነበር፣

> "የሕሊና ሰላም ለማግኘት ለራሴ በብዙው እያዳላሁ የሚቻለኝን ያህል በግሌ (ችግረኞች) መርዳቴ አልቀረም ነበር፡፡ (ባለቤቴና እኔ) የማናውቃቸውን ሰዎች በትንሽ ፍራንክም ቢሆን ደሞዝተኞች ለማድረግም ሞክረናል፡፡ ባጋጠመኝ ቁጥር መሻሻል እንደሚያስፈልገን ድምጼን ሳላሰማ አላለፍኩም፡፡ ይህ ይበቃ ነበር ወይስ ያለኝን (ደሞዜን) ሁሉንም ለሌለው እኩል አካፍዬ፥ ከአቅሜ በታች መኖር ነበረብኝ? ወይስ በእድሜ ልኬ የተዘጋጀሁበትን ትቼ ሥር ነቀል ለውጥ ለማድረግ የተዘጋጁ ኅቡእ ድርጅቶች ፈልጌ አባል መሆን ነበረብኝ?"

ይኸንን ነው ዶክተር ታደለ ያላሰብኩትንና ያላለምኩትን ትርጉም የሰጡብኝ፡፡ "እያስተማርኩና እየጻፍኩ ወገኖቼን አገሬን ለመርዳት ካልቻልኩ የተዘጋጀሁበትን ትቼ በሌላ መንገድ ብረዳ ይሻል ይሆን ወይ" ብዬ አሰብኩ እንጂ፥ እሳቸው እንዳሉት "ሃገሬን እያስተማርኩና እየጻፍኩ ለመኖር ብመጣ ልብሴን ከላዩ ገነጣጥለው ሊወስዱት ይጋበዛሉ፡፡ ሃገርን ጥሎ መኖር የሚል ድምዳሜ . . . ይከተላል" ያሉትን እንኳን ላስበው በአእምሮዬ አጠገብ ሽው ብሎም እንኳ አያውቅም፡፡ ሀገር ጥሎ የመሄድ ሐሳብ ቢኖረኝ ኖሮ ቀደም ብሎ ገና ጠላት ጤና ሳይነሣኝ ዕድሉ አጋጥሞኝ ነበር፡፡ ወደ አሜሪካ ከሚያመጣኝ አይሮፕላን ላይ ስገባ የተሰማኝን ስሜት በጥቂቱም ቢሆን እመጽሐፉ ውስጥ ገጽ 229 ላይ ልገልጸው ሞክሬያለሁ፡፡ ዶክተር ታደለ ያንን ገጽ ልብ ብለው አላነበቡት ይሆናል፡፡ ዶክተር ታደለ ምንጫቸው የኔ መጽሐፍ እስካልሆነ ድረስ ሐሳባቸውን መግለጽ መብታቸው ነው፡፡

ጸሐፊው እንዲህ እንዲህ ቢሳሳቱም የእኔን የዕውቀት ደረጃ ከፍ አድርገው የሚገምቱት መሆኑን አይቻለሁ፡፡ የኢትዮጵያን ታሪክ ቆነጠርኩለት እንጂ እሳቸው እንደሚሉት በባሕር በሚገመት ደረጃ አላነሣሁለትም፡፡ ለማንኛውም ለቃላት ችሮታቸው ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

አሁን እንግዲህ ሁላችንንም ወደሚያሳስበን ቁም ነገር ልምጣ፣ እሱውም ልጆችን እውጪ አገር የማሳደጉ ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩ ስሜት ስለሚነካ፥ እንደመሰለ፥ እንደታየ፥ መተቸት ቀላል አይደለም፣ ሰው ያስቆጣል፡፡ ሆኖም፥ በእኔ አስተያየት ልጆችን ማሳደግ የሚገባው ለሚኖሩበት በወሰኑት አገር ሥርዓተ ትምህርት ነው፡፡ ይኸም የሀገሩን ቋንቋ ማለዘብን ይጨምራል፡፡ ሥርዓተ ትምህርቱ የተማሪው እራስ ሐሳብ እንዲያፈልቅ፥ ያፈለቀውን ሐሳብ በግልጽና ሰሚን በሚጥም ቋንቋ እንዲያስተላልፍ የሚያሠለጥን ነው፡፡ ትምህርት ኑሮን ማሸነፊያ መሣሪያ ስለሆነ፥ ልጆቻችንን ኑሮን የሚያሸንፉበትን የሰላ መሣሪያ ማስታጠቅ ይኖርብናል፡፡ ኑሯቸውን ኢትዮጵያ ለማድረግ ወደ ኢትዮጵያ የሚመለሱ ልጆች ሁሉ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያገለግላቸውን ቋንቋ (በተለየ አማርኛን) ጠንቅቀው ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ከየትም አገር ወደ አሜሪካ መጥተው በግድም በውድም በአሜሪካ የሚኖሩ

ግን፥ የአሜሪካንን ትምህርት በሀገሩ ቋንቋ (በእንግሊዝኛ) ጠንቅቀው ማወቅ ያስፈልጋቸዋል፡፡

የናት አባትን ቋንቋ ትቶ በመንግሥት ቋንቋ ማደግ የማይገቱት፥ ሊገቱትም የማያስፈልግ የታሪክ ሂደት እንጂ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥም ሲፈጸም የኖረ ነው፡፡ ከብሔራዊ አንድነት የሚደረሰው በዚህ መንገድ በመሄድ ነው፡፡ የትግሬ ወያኔዎች አማርኛ እንዳይስፋፋ ሲያደርጉ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የሚቃወሙት ለአማርኛ ተቆርቁረው ሳይሆን ሀገሪቱ አንድ የምትሆንበትን መንገድ ሁሉ ሲዘጉ በማየታቸው ነው፡፡

ከየቦታው እየመጡ አሜሪካ የሚሰፍሩ ስደተኞች የትውልድ ሀገራቸውን ቋንቋ የሚማሩት ለግላቸው፥ ለትዝታው ብቻ ነው እንጂ በኑሯቸው እንዲጠቀሙበት ወይም የትውልድ አገራቸው እንድትጠቀምበት አይደለም፡፡ እንዲህ ያሉ ስደተኞች የትውልድ አገራቸውን ቋንቋ አለመማራቸው ትተውት የመጡትን አገር ይጎዳል የሚል እምነት የለኝም፡፡ አሜሪካ እየኖሩ አማርኛ አለመናገራቸው እንዴት ነው የማይኖሩባትን የትውልድ አገራቸውን የሚጎዳው? ማሰብስ ለእነዚህ ግፋ ቢል ከአንድ ሚሊዮን ለማይበልጡ ኑሯቸውን ከኢትዮጵያ ውጪ ለአደረጉ ዜጎች ሳይሆን፥ ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖሩ መንግሥት አገሪቱን ከጥንት ጀምሮ የሚያስተዳድርበትን ቋንቋ (አማርኛን) እንዳይማሩ ወያኔ ስላሰናከላቸው ከሃያ ሚሊዮን ስለሚበልጡት ኢትዮጵያውያን ነው፡፡

ሥር መሠረታቸው ኢትዮጵያ የሆነች የአሜሪካ ነዋሪዎች ኢትዮጵያን የሚረዷት ከአሉበት ሀገር በሚያገኙት ሀብት፥ ዕውቀትና የፖለቲካ ኃይል ነው፡፡ ለልጆቻችን ማስያዝ ያለብን የታሪክ ሰዎች መሆናቸውንና የትውልድ ሀገራቸው የእነሱን እርዳታ የምትጠብቅ መሆኗን ነው፡፡ እነዚህ አዲስ ኢትዮ-አሜሪካውያን በጉዲፈቻ የሚጎርፉትን ሕፃናት ጨምሮ ቊጥራቸው እየበዛ ስለሚሄድ፥ ስለትውልድ ሀገራቸው ጉዳይ በአሜሪካን የፖለቲካ ሰዎች ላይ ተጽእኖ ሊያደርጉ፥ ከዚያም አልፈው፥ እነሱ ራሳቸውም የአሜሪካ የፖለቲካ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በዚህ ረገድ ነው ኢትዮጵያን ሊጠቅሟት የሚችሉት፡፡

ልጆች የትውልድ ሀገራቸውን ባህል መማር የለባቸውም አልልም፤ ወላጆቻቸው ዕውቀቱ ለልጆቻቸውና ለሀገር የሚያስፈልግ መሆኑን ካዩ ማስተማር ይኖርባቸዋል፡፡ "አማርኛ አልረሱም" ማለትም ደስታና ኩራት ይሰጣል፡፡ ጉዳዩን ሳይመረምሩ አማርኛ አላወቃችሁም ከሚል ነቀፌታ መግባት ግን ልክ አይመስለኝም፡፡ ኢትዮጵያ ብንኖር ምኞቴ ይፈጸምልኝ ነበር፤ ከኢትዮጵያ የማበልጠው መኖሪያ የለኝም፡፡ ይህ የማይቻል ከሆነ፥ አሜሪካ ለመኖር ከተገደድን፥ ልጆቻችንን ከአሜሪካ ኑሮ ከቁንጮው ላይ ልናስቀምጣቸው በመቻላችን ኢትዮጵያን የጎዳን አይመስለኝም፡፡

ለመደምደሚያ፤ አንድ በትምህርቱ ከዓሥራ ሁለተኛ ክፍል በላይ ያልሄደ ወጣት ዘመድ አለኝ፡፡ በተገናኘን ቊጥር እኔንና አባቱን በአሽሙር ለመንካት፥ "ኢትዮጵያ ያስተማረቻቸው ዶክተሮች ሁሉ ተመልሰው ያስተማረቻቸውን ሀገራቸውን መርዳት አለባቸው" ይለኛል፡፡ አሽሙሩ ቢሰለቸኝ፥ "በአንተ የዕውቀት ደረጃ ያለ ሰውስ አገሩን መርዳት አይችልም ወይ? አንደኛ ደረጃ ማስተማርም አገር መርዳት ነው፤ ታዲያ እዚህ ምን ታደርጋለህ?" ብዬ ጠየቅሁት፡፡ ከዚያ ወዲህ አሽሙሩን ተጠቅሞበት አያውቅም፡፡ አሜሪካ የሚኖሩት የዶክተር ታደለ ዕውቀትማ (ምናልባት የልጆቻቸውም) በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያን ብዙ የሚጠቅም ነው፡፡